# ፀንተህ ቁም አንበሳ!



የጨካው ባለቤት ንጉሱ ማን ሆኖ፣
ውጣ ተዚህ አለ ጅብ እግሩን አንስቶ!

ይመስክር ሸበሌ ገናሌና ባሮ፣
ቃሉን ይሥጥ ዝቋላ ባቱና ጭላሎ፣
አንበሳ ጠብቆት የኖረው ተከብሮ!

ይናገር ጉራቻ ይመስክር የረርም፣
ያየው ባራት ዓይኑ አንበሳ ሲፋለም።

ይፈተሽ መሬቱ ይቀመስ አፈሩ፣
ምን ያንበሳን ደም የኖረው ተክብሩ!

እባብ ሱስ አቅምሶ በአውሬ አስከብቦሃል፣
አግስተህ መነሻህ ይኸ ወቅት ሆኗል።

የቅጥፈት ድመራው ቱልቱላው አልበጀም፣
ጅብ በመለማማጥ አደብ ገዝቶ አያውቅም።

የሰው ልጅ ዘቅዝቆ አንገት እሚያርድ ጅብ፣
ጥርሱ ታልወለቀ መዘንቸር አይተውም!

ውሻ ሲያባርርህ ማፈግፈግ ተጀመርክ፣
ገነት ብትገባም ተከትሎ አይለቅህ!

ተደረጃ በቅሎ በልግ የሰጠው ጫቅማ፣
ጠግቦ ወቢ ተፋ በወይራና ዋንዛ!

የአንበሳ ቁሶቹ አቡኑም ጳጳሱም፣
ሀጅውና ሼሁ መነኩሴው ዲያቆኑም፣
እንደ ትጉ እረኛ ተበጎችህ ጋር ቁም፣
ልጆች አስፈጅተህ ኑሮህ ኑሮ አይደለም።

እንደሚታወቀው ትልቁ መጣፍም፣
ሰይጣን ሲያጣምምህ ፊትህን ስጥ አይልም።

የአንበሳ ልጅ ሁሉ ባለም ዙሪያ ሰፍርህ፣
እንደ አሳማ በሆድ በከርስህ ተገዝተህ፣
ተማይቀረው ዓለም በመጓዝ ላይ ያለህ፣
መኖር አትበለው ዘርህን አስጨፍጭፈህ!

አንበሳ ሆይ ፍልሚያ ላንተ አዲስ አደለም፣
ከቱርክ ከርከሮ ከሮም ጅብ አይበልጥም!

እንደ ቅድመ-አያትህ እንደ ራስ አንበሳ፣
ነፋስ ሳታስገባ በአንድነት ተነሳ!

ጊዜ ይፈትናል ጣድቅና ጀግና፣
ድል ያባቶችህ ነው ፀንተህ ቁም አንበሳ!

በላይነህ አባተ (abatebelai@yahoo.com)
ጥቅምት ሁለት ሺ አስራ ሁለት ዓ.ም.